ውበየወ/መ/ቁጥር 168342

የልደታ ምድብ 5ኛ ወንጀል ችሎት

ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ አቶ ሞገስ ይልማ አለማየሁ - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቅጣት ለመወሰን ሲሆን በዚሁ መሰረትም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትህዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል፡፡

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው፡፡ የደረጃ አወሳሰኑም ማከበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል፡፡

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው በምሽት መሆኑ፤ ወንጀሉን የፈፀመው ገዳይ መሳሪያ የሆነውን ጩቤ ይዞ በመሆኑ፤ የግል ተበዳይንም ብቻዋን እንደምትኖር እና ሌላ ወንጀሉን ሊከላከልላት የሚችል ሰው አለመኖሩን አውቆ የፈፀመው በመሆኑ የወንጀል ደረጃው ከባድ ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ከባድ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከዘጠና አምስት ቀን እስከ አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ቀን ተኩል ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት አንድ መቶ ሃያ ቀን መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል፡፡

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሦስት ወር ከአስራ አምስት ቀን እስራት ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ተከሳሽ ድርጊቱን የፈፀመው በምሽት መሆኑና የጦር መሳሪያ መጠቀሙ አደገኛነቱን ስለሚያሳይ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት ያመለከተ ሲሆን፤ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሐ) የወንጀል አፈፃፀሙ አኳኋን በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ወይም ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሳሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሳሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ በማለት የተደነገገ ሲሆን ፍ/ቤቱም እንደመረመረው ተከሳሽ ድርጊቱን የፈፀመው በቃላት በመናገር በዛቻ ሲሆን፤ የያዘውን ጩቤ ወንጀሉን ለመፈፀም ተጠቅሞበታል ለማለት ስለማይቻል እንዲሁም ድርጊቱ የተፈፀመው ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ስለሆነ፤ ይህ ሰዓት ደግሞ ሌሊት ስለማይባል የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶቹን ፍ/ቤቱ አልተቀበላቸውም፡፡

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ላይ በተገለፁት መሰረት አላቀረበም፡፡ ሌላው ባለትዳር ነኝ፤ በጥበቃ ስራ በወር ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) እየተከፈለኝ እኖራለሁ ቢልም ባለቤቱ ሥራ እንደሌላትና በእሱ ገቢ ብቻ እንደምትኖር በማስረጃ አስደግፎ ያላቀረበ በመሆኑ እንደ ቅጣት ማቅለያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ በተመለከተው ፈቀደ ስልጣን/range/ ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ባለመኖሩ በሦስት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሹ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ
   የተወሰነው የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡

2ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ፡፡

3ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል፡፡

4ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡